**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢ.ጋን)**

ሚያዚያ 22፣ 2004ዓም

# በጋምቤላ የፓኪስታን ተወላጆች ተገደሉ

## ሕዝቡ "እንደ ኦጋዴን ዓይነት በቀል ይፈፀማል" የሚል ስጋት ውስጥ ገብቷል

በጋምቤላ ማንነታቸው ያልታወቀ ታጣቂዎች የሳዑዲ ስታርን ሜካናይዝድ እርሻ ቢሮ፣ የሠራተኞች መኖሪያና ማደሪያ ካምፕ በመግባት ጥቃት መፈፀማቸው ታወቀ። በጥቃቱ አራት የፓኪስታን ተወላጆችን ጨምሮ አስር ሰዎች ሲገደሉ ከአስራ አንድ በላይ ቆስለዋል። የክልሉ ነዋሪዎች የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ በኦጋዴን ንጹህ ዜጎች ላይ የፈፀመውን ዓይነት የበቀል ርምጃ ይወስድብናል በሚል ስጋት ላይ መውደቃቸውን ተናግረዋል።

ቅዳሜ ሚያዚያ 20፤2004ዓም አመሻሽ ላይ በግምት አስራ አንድ ሰዓት ከሰላሳ አካባቢ የተፈፀመውን ጥቃት አስመልክቶ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢ.ጋን) የመረጃ ምንጮች ከስፍራው በላኩት ዘገባ እንዳስታወቁት ጥቃቱን የፈፀሙት ታጣቂዎች የሳውዲ ስታር እርሻ ካምፕ የተቆጣጠሩት ለአስራ አምስት ደቂቃ ብቻ ነበር።

የአኢ.ጋን የመረጃ ሰዎች የዓይን እማኞችን በመጥቀስ እንደዘገቡት "ሽፍታ" በሚል ስያሜ የሚጠሩት ታጣቂዎች ንብረትነቱ የሼኽ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ የሆነውን የሳዑዲ ስታር እርሻ ሁለገብ ካምፕ ያለአንዳች ችግር ዘልቀው ከገቡ በኋላ የኮማንዶ ስልት በተሞላበት ቅልጥፍና እና ፍጥነት በመከፋፈል የእርሻውን ሥራ ማከናወኛ ቢሮ፣ የዋና ዋና ሰራተኞች መኖሪያ፣ ካፊቴሪያና የተመረጡ ቦታዎችን በመቆጣጠር ተግባራቸውን አከናውነዋል። ታጣቂዎቹ ካምፑን ተቆጣጥረው ምን እንዳከናወኑ በዝርዝር ባይታወቅም አራት ከፍተኛ የእርሻ ኤክስፐርት የሆኑ የፓኪስታን ዜጎችን ገድለዋል። ሶስት ክፉኛ አቁስለዋል። አራት ኢትዮጵያዊ ሠራተኞችና አንድ የአኙዋክ ተወላጅ የጥበቃ ፖሊስ ሲገደሉ ስድስት የሚሆኑ ደግሞ ክፉኛ ቆስለዋል። የአኢ.ጋን መረጃ አቀባዮች እንዳሉት ይህ ሁሉ ሲሆን በካምፑ ቅርብ ርቀት የሚገኙት የመከላከያ አባላት ድጋፍ ለመስጠት አልፈቀዱም። ተኩስ እየሰሙ ዝምታን መርጠዋል።

ብዛታቸውና ማንነታቸው የማይታወቀው ታጣቂዎች ጥቃቱን አከናውነው ከተሰወሩ በኋላ የመከላከያ አባላት ስፍራውን ሲቆጣጠሩ ያገኙት ሙትና ቁስለኛ ብቻ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። ያደረጉት ነገር ቢኖር ህይወታቸው ያለፈውን አምቡላንስ በመጥራት ወደ ጋምቤላ ከተማ ማጓጓዝ ሲሆን የቆሰሉትም የመጀመሪያ ርዳታ እንዲያገኙ ወደ አቦቦ ሆስፒታል ማድረስ ብቻ ነበር። ቁስለኞቹ ወደ ጋምቤላ ሆስፒታል እንዲወሰዱ ከተደረገ በኋላ ለተሻለ ህክምና ወደ መቱ መወሰዳቸውን የሆስፒታል ምንጮች ጠቁመዋል። ምን ያህሉ እንደተወሰዱ ግን አላብራሩም።

ጥቃቱን ተከትሎ በአፋጣኝ የተወሰደው ርምጃ እርሻው አካባቢ የሚኖሩትን ነዋሪዎችና ሰራተኞች ሙሉ በሙሉ አካባቢውን እንዲለቁ ማድረግ እንደነበር ያስታወቁት ምንጮቻችን፣ ከሰባት መቶ በላይ የእርሻው ሠራተኞች በፍርሃቻ ሳቢያ መኖሪያቸውን እንዲለቁ ተደርጓል። ከዚህም በተጨማሪ የክልሉ ፕሬዚዳንት አቶ ኦሞት ኦባንግና የደኅንነት ኃይሎች ወደ ስፍራው ደርሰው ህዝቡን በመሰብሰብ "እንዴት ይህ ሁሉ ፖሊስና ሚሊሺያ እንዲሁም ጥብቅ የካምፑ ጥበቃ ኃይል እያለ ሽፍቶቹ ይህንን ያህል ግድያና ጥፋት ሊያደርሱ ቻሉ? እንዴትስ ዘልቀው ገቡ?" በማለት ህዝቡና የአካባቢው ሚሊሺያ መልስ እንዲሰጡ ግምገማ መሰል አውጫጪኝ ለማድረግ ሞክረዋል።

ቁጥራቸው ከአስር በላይ የሚሆን የአካባቢው ተወላጅ የፖሊስ ኃይል አባላት በጥርጣሬ መታሰራቸውን ያመለከቱት የመረጃ ሰዎቻችን፣ መሳሪያ ያላቸው የአካባቢው ተወላጆችም የመከላከከያ ሰራዊት በጅምላ እየወሰደ ያለውን እስርና እንግልት በገሃድ እንደተቃወሙ አመልክተዋል። አያይዘውም "ህዝቡን ማሰር አትችሉም" በማለት ተቃውሞ በማስነሳታቸው ሳቢያ አለመግባባት መካረሩን ጠቁመዋል።

ከተሰብሳቢዎች መካከል አንድ አባት "ጫካ ግቡና ሽፍቶቹን ፈልጉ፤ እኛ ምን እናውቃለን? ለምንስ ታስጨንቁናላችሁ?" በማለት መናገራቸው የደህንነት ሰራተኞችን ማበሳጨቱን ያስረዱት የጋራ ንቅናቄያችን ሰዎች፣ ታጣቂዎቹ በአካባቢው ከሚኖሩት አኙዋኮች ጋር ግንኙነት አላቸው በሚል በሳውዲ ስታር እርሻ አካባቢ ነዋሪዎች ላይ እየተወሰደው ያለው የማፈናቀል ተግባር በክልሉ ያለውን ችግር ያባብሰዋል የሚል ስጋት እንዳለ ገልጸዋል።

ጥቃቱ ከተከናወነ በኋላ ተሽከርካሪዎችን በማስቆም የፍተሻ ስራ መጠናከሩን ያመለከቱት የዓይን እማኞች፣ የመከላከያ ነፍጥ አንጋቾች ከጋምቤላ ወደ አቦቦ እየተጓዘ ያለ አውቶቡስ በማስቆምና ውስጥ ያሉትን ተሳፋሪዎች በማስወረድ ፈርጣማ ሰውነት ያላቸውን ወጣቶች መርጠው "ለምርመራ" በሚል ወሰደዋቸዋል። ሴቶችና አዛውንት ተሳፋሪዎችን ደግሞ በመጡበት አውቶቡስ ወደ ጋምቤላ ከተማ እንዲመለሱ ተደርገዋል። ፍተሻውና ብርበራው ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ሰዓት ድረስ አልቆመም።

አቶ ኦሞት ላይ ግምገማ ከተካሄደና **"እኔ ከታሰርኩ አቶ መለስም መታሰር አለባቸው"** በማለት ከተናገሩ ጊዜ ጀምሮ በጋምቤላ ግድያ፣ እስር፣ አፈና፣ ጭከና፣ ማፈናቀልና በንፁሃን ዜጎች ላይ እየደረሰ ያለው ግፍ እየተባበሰ መምጣቱ እንዳሳሰበው የጋራ ንቅናቄያችን በተደጋጋሚ መግለፁ ይታወሳል። በንፁሃን ዜጎች ላይ እየደረሰ ያለው ግፍ እንዲያበቃ መደረግ ያለበትን ሁሉ ከማድረግ በተጨማሪ ድርጊቱን በማውገዝ ለፍትህ ወዳጆች ሁሉ በተደጋጋሚ ጥሪ ሲያቀርብ እንደነበርም አይዘነጋም።

ከጋምቤላ የጋራ ንቅናቄያችን የመረጃ ሰዎች ያሰባሰቡት መረጃም እንደሚያመለክተው በክልሉ ሰላም የለም። ከዜጎቹ ይልቅ መሬታቸውንና ሃብታቸውን በመሸጥ የውጭ ምንዛሪን የሚያስበልጠው የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ፣ አግባብነት በሌለው ኢንቨስትመንት ስም የሚሰበስበው ዶላር እንዳይቆምበት በመስጋቱ፣ በተፈጠረው የሰላም መታጣት የተነሳ የዶላር ምንጩ እንዳይነጥፍና ኢንቨስተሮች በዚሁ አለመረጋጋት ምክንያት ክልሉን እንዳይለቁ በኦጋዴን ንጹሃን ኢትዮጵያውያን ላይ የተወሰደው የጅምላ ጭፍጨፋ ዓይነት የበቀል ርምጃ ይወሰድብናል የሚል ስጋት ያላቸው እየተበራከቱ ነው።

ኦጋዴን በነዳጅ ፍለጋ ጣቢያ ውስጥ የኦጋዴን ነጻ አውጪ በመግባት የቻይና ዜጎችና በርካታ ኢትዮጵያዊያን ላይ ጥቃት መፈጸሙን ተከትሎ የክልሉን ሰላማዊ ሰዎች በመክበብ፣ ከማንኛውም አገልግሎትና የግብይት ስርዓት በመለየት የተፈፀመባቸውን የጅምላ የበቀል ርምጃ ያስታወሱት የጋምቤላ ነዋሪዎች፣ **"ዜጎች፣ ወገኖች፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት፣ ዓለም አቀፍ ተቋማትና ለጋሽ አገሮች በቅርብ ተከታተሉን"** የሚል ድምጽ ማሰማታቸውን የንቅናቄያችን የጋምቤላ የመረጃ ሰዎች ሪፖርት ያስረዳል።

**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)**
**የሚዲያና ሕዝብ ግንኙነት ግብረኃይል**

---

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን) የሚዲያና ሕዝብ ግንኙነትን (media@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን(www.solidaritymovement.org)በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡*

